ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ጥቅምት 2001 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 22

# የምግብ ዋስትና ስትራቴጂና ምርት ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር በኢትዮጵያ

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው።

❋❋❋

- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል።

❋❋❋

- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል።

❋❋❋

- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል።

❋❋❋

- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መስንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን።

## መግቢያ

የምግብ ዋስትና እጦት ችግር በኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወይም ስር የሰደደ ነው። ስር የሰደደው ችግር ቤተሰቦች ያለ በቂ ምግብ ለረጅም ጊዜ በየዓመቱ የሚቸገሩበት ሲሆን ጊዜ ያዊው የምግብ ዕጥረት ችግር ደግሞ በድንገተኛ ተፈጥሮአዊ (ዝናም ዕጥረት) ወይም ሠው ሰራሽ (ገበያ ነክ) ችግር የተነሳ የሚከሰት የምግብ ዕጥረት ነው። በኢትዮጵያ ወደ 50% የሚደርስ ሕዝብ በጊዜያዊም ሆነ ስር በሰደደው የምግብ ዕጥረት ችግር ውስጥ የሚኖር ነው። ለችግሩ ተጋልጠው ከሚገኙት ውስጥ አብዛኞቹ አነስተኛ የመሬት ይዞታ ያላቸው፣ እማወራ ቤተሰቦች፣ በሬ የሌላቸውና በዕድሜ የገፉ ሰዎች ናቸው።

የምግብ ዋስትና ዕጦት መንስኤዎች የተሳሰሩ የረጅም ጊዜ (structural) እና ጊዜያዊ ባህሪ ያላቸው ናቸው። መንስኤዎቹም ምርታማ ያልሆኑ ግብርና ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፣ የተፈጥሮ አከባቢ መከላት (environmental degradation)፣ የሕዝብ ብዛትና የተስተካከለ የዝናም መጠንና ስርጭት ዕጦትን ያካትታሉ።

ከዚህ በመነሳት በአገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ቀጣይና ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ የምግብ ዋስትና ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና መርሐግብሮች መንደፍና ሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል።

የዚህ ጽሑፍ ዓላማም ያሁን ጊዜን የኢትዮጵያን የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ እና በመተግበር ላይ የሚገኘውን የምርት-ተኮር ሴፍቲ-ኔት መርሐግብር ጥንካሬአቸውንና ደካማ ጎናቸውን ቃኝቶና አጢኖ የማሻሻያ ሀሳቦች ለመሰንዘር ነው። ይህን ዓላማ ለማከናወን ፀሐፊው የተለያዩ አግባብ ያላቸውን ዋቢ ጽሑፎችና የሥራና ግምገማ ሪፖርቶችን ዳስሷል።

## 1. የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ

ሥር የሰደደውን የምግብ ዕጥረት ችግር ለመቅረፍ የኢትዮጵያ መንግሥት ላለፉት 15 ዓመታት የተለያዩ ፖሊሲዎችንና መርሐግብሮችን ነድፏል። ከነዚህም ውስጥ እ.ኤ.አ. 1996 ዓ.ም. ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀርፆ በ2002 የተሻሻለው የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ይገኝበታል። የዚህ ስትራቴጂ ዋነኛ ዓላማ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ነው።

### 1.2. የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ዋና ዋና ስልቶች

በምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ሰነድ ውስጥ የተጠቀሱት ዋነኛ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ ስልቶች አራት ናቸው። እነርሱም:-

ሀ) የምግብ ምርትን የማሳደግ መርሐግብር:- ምርትንና ምርታማነትን የሚያሳድጉ ዘዴዎችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የምግብ አቅርቦትን (supply) ከፍ ማድረግ፣

ለ) የሰፈራ መርሐግብር:- በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ ድሃ ገበሬዎችን እና ሰብልንና እንስሳትን አጣምረው የሚያመርቱ (Agro-pastoral) ችግረኛ አምራቾችን በክልላቸው ውስጥ በሚገኙ ጥቅም ላይ ባልዋሉ መሬት ላይ ማስፈር፤ ይህም የመሬት ይዞታ አናሳነትንና የአከባቢ የተፈጥሮ ሀብት ክለትን በመቀነስና የተሻሻለ የኑሮ ሁኔታ ለሰፋሪዎች በመፍጠር ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ ይገመታል።

ሐ) የገቢ ምንጮች ማስፋፊያ መርሐግብር:- የምግብ ዋስትናን በገጠሩ ለማረጋገጥ በሰብልና እንስሳት ምርት ሥራ ላይ ብቻ መገደብ በቂ አይደለም። ስለሆነም መርሐግብሩ ከሰብልና እንስሳት ማምረት ሥራ ውጭ የገቢ ምንጮችን በሚፈጥሩ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች (ንግድ፣ የእጅ ሙያ ሥራዎች ወዘተ) ውስጥ መሳተፍን ይተልማል፤ ያበረታታልም።

መ) ምርት-ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር:- ይህ የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ አንዱ መንገድ ሲሆን ትኩረቱም ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና እጦት ውስጥ በሚገኙ ስፍራዎችና ቤተሰቦች ላይ ነው።

### 1.3 የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ እርምጃዎች

የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ እርምጃዎች በቂ እርጥበት ባለበት ስፍራዎች፣ የእርጥበት ዕጥረት በሚታይባቸው ቦታዎችና በቆላማ አርብቶ አደር አካባቢ እንደሚተገበሩ ሰነዱ ያስረዳል:: በነዚህ ስፍራዎች የሚወሰዱት እርምጃዎችም በሦስት ዘርፎች ይከፈላሉ:: እነሱም-

- ምርትን መጨመር
- የመግዛት አቅምን መገንባት
- ድንገተኛ አደጋን የመቋቋም አቅምን ማጎልበት

#### 1.3.1 የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ እርምጃዎች በቂ እርጥበት ባላቸው ስፍራዎች

የመርሐግብሩ ሰነድ እንደሚገልጸው በነዚህ ስፍራዎች በዝናም ላይ የተመሠረተውን ከእጅ ወደ አፍ የግብርና ሥርዓት ወደ አዳጊ ገብያ-ተኮር ግብርና ሥርዓት መለወጥ የስትራቴጂው ዋነኛው አቅጣጫ ነው:: የመስኖ ግብርና ውሃ-ገብ በሆኑ ስፍራዎች ማስፋፋትና በሕዝብ ብዛት ከተጨናነቁ ስፍራዎች ላይ አርሶአደሮቹን በፈቃደኝነት በዚያው ክልል አመቺ በሆኑበት ስፍራዎች ላይ ማስፈር በሰነዱ ውስጥ የተጠቀሱ እርምጃዎች ናቸው::

#### 1.3.2 የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ እርምጃዎች በዕርጥበት አጠርና በቆላማው አርብቶ አደር ስፍራዎች

ለእነዚህ አካባቢዎች ዋነኛው የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ መንገድ የከፊል ሰብል፣ ከፊል እንስሳ አምራቾችን (agro-pastorlists) እና የቆላማው አርብቶ አደሮችን የመግዛት አቅም ሊያጎለብቱ በሚችሉ ገቢ በሚያስገኙ ተጨማሪ ሥራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ማመቻቸት ነው:: እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብትን አጠቃቀም በተገቢው መምራት፣ ዘለቂነት ያለው የቆላማ ግብርና ሥርዓትን ማሳደግና የእንስሳት ዕርባታን ማጠናከር ሊተኮሩባቸው የሚገቡ ሥራዎች መሆናቸውን ሰነዱ ይገልፃል:: ስትራቴጂው የቆላማ አርብቶ አደር ልማትን በሚመለከት ሰፋፊ የእንስሳት ርቢ (ranches) እና በአንድ ቦታ በቋሚነት ሰፍሮ (sedenterization) ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ስርዓት መመስረት የወደፊት አቅጣጫ እንዲሚሆን ይጠቁማል:: እዚህ ላይ የዚህ ጽንሰ ሀሳባዊ አካሄድ ተጨባጭ ከሆነው የቆላማው አርብቶ አደር ልማት ሥርዓት (system) ፣ ባህል፣ አኗኗር፣ የለውጥ ሂደትና የአካ ባቢው ተፈጥሮአዊ ባህርያት አኳያ መመርመርና በዓይነት ለይቶ በአጭርና ረጅም የጊዜ ርዝመት አማራጭ መንገዶችን ባካተተ መልኩ መጤን ይገባዋል::

### 1.4 ለስትራቴጂው ተግባራዊነት የሚያስፈልጉ ሁኔታዎችና አገልግሎቶች

የምግብ ዋስትናን በምርት ወይም አቅርቦት አኳያም ሆነ የመግዛት አቅም በመገንባት ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ሁኔታዎችንና አገልግሎቶችን ማደራጀትና ማመቻቸት ተገቢ ነው:: ስትራቴጂው ትኩረት የሰጣቸው አስፈላጊ ሁኔታዎችና አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው::

ሀ/ ዋስትና ያለው የመሬት ሥሪት፣

ለ/ አመቺ የንግድና ገብያ ሁኔታዎችና አገልግሎቶች (ለምሳሌ ደረጃ መዳቢና ጠባቂ፤ መጓጓዣ)፣

ሐ/ የግብርና ምርምርን መረብ ማጠናከር፣

መ/ የግብርና ግብአቶች አቅርቦትን ማመቻቸት፣

ሠ/ የገጠር መንገድ መረቦችን ማጎልበት፣

ረ/ መርሐግብሮች የሥነፆታ ምልከታ እንዲኖራቸው ማድረግ፣

ሰ/ የቤተሰብ እቅድንና ትምህርትን ማስፋፋት፣

ሸ/ ኤድስን የመቆጣጠርና የመከላከል ሥራዎችን ከምግብ ዋስትና መርሐግብሮች ጋር ማቀናጀት::

### 1.5 ሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴን የሚረዱ ተግባሮች

የስትራቴጂው ሰነድ እንደገለጸው የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተለያዩ የኢኮኖሚ ሥራዎችን ማስፋፋትና ለሥራዎቹ የሚረዱ እገዛዎችን ማደራጀት በጣም ጠቃሚ ነው:: በዚህ ረገድ ጥቃቅንና አነስተኛ የኢኮኖሚ ድርጅቶችን (enterprises) ማስፋፋትና በምርትና ግብአት ገበያዎች (የንግድ ሥራዎች) የተሻለ ሚና እንዲጫወቱ ማገዝ፣ ግብርና ነክ የሆኑ አዳዲስ የውጭ ምርቶች እንዲበራከቱ ማገዝ፤ የሥራ ዕድልን ከመንግስትና ሕዝብ በሚገኝ ሀብት መፍጠርና ተቋማዊ ጥንካሬንና ትስስርን ማጎልበትና አቅምን መገንባት (ለምሳሌ የገበሬ ማህበራትን፣ የሕብረት ሥራ ማህራትን ማደራጀት፤ የማቀድ፣ የመቆጣጠርና የመገምገም አቅምን መገንባት) ከሚያስፈልጉ እርምጃዎች ጥቂቶቹ ናቸው::

### 1.6 ድንገተኛ አደጋን የመከላከልና የመቋቋም ችሎታን ማዳበር

የምግብ ዕጥረትን በቤተሰብም ሆነ በብሔራዊ ደረጃ የመቋቋም አቅም ባሁኑ ጊዜ አገሪቱ ስለሌላት ለዘለቄታው በቤተሰብ ሆነ በአገር ደረጃ አቅሙ እስኪፈጠር ለሚቀጥለው አጭር ጊዜ ዕርዳታ አስፈላጊ ይሆናል:: የሚገኘውን የድንገተኛ አደጋ መከላከያና መቋቋሚያ ዕርዳታን አገሪቱ ባግባቡ የመምራት አቅም ማጎልበት ይኖርባታል:: በዚህ ረገድ ከሚያስፈልጉ አቅሞች ውስጥ መጠባበቂያ እህል ማስቀመጥ፣ ምግብንና ዕርዳታን በቅልጥፍና ማሰራጨት፣ አስቀድሞ መጠንቀቅና ማስጠንቀቅ ይገኙበታል::

### 1.7 የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ጥንካሬና ድክመት

በመሠረቱ አንድ የተቀናጀ የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መነደፉ በራሱ በጎ ጎን ነው:: ከዚህም በተጨማሪ የችግሩ ዋነኛ ሰለባ የገጠሩ ሕዝብ መሆኑን ተገንዝቦ ስትራቴጂው ገጠር-ተኮር መደ

ረጉና፣ የምግብ ዋስትና ክስተት ባለብዙ ዘርፍ መሆኑን ተመልክቶ ከግብርና ውጭ የሆኑትን ስልቶችን አካቶ መነሳቱ ጠንካራ ጎኖች ናቸው:: ይሁን እንጂ ስትራቴጂው ሕይወት ኖሮት ተ ጨባጭ ጉዳዮችን እያገናዘበ እንዲጓዝ የሚከተሉትን ዋና ዋና ድክመቶች ማረም የግድ ይላል::

ሀ) በቤተሰብ ውስጥ ያለው የተዛባ የምግብ አደላደል የተወሰኑ አባሎችን (ለምሳሌ ሕፃናትንና ሴቶችን) ለምግብ ዕጥረት ስለሚያጋልጣቸው ጉዳዩ ትኩረት ይሻል::

ለ) ለምግብ ዋስትና ዕጥረት የተጋለጡ ቤተሰቦች የሚገኙት በዝናም-አጠርና ቆላማ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በቂ እርጥበት ባላቸው አካባቢዎችና በከተማም ስለሆነ እነዚህ ስፍራዎችና ቤተሰቦች የስትራቴጂውን ትኩረት ይፈልጋሉ::

ሐ) ስትራቴጂው የሲቪል ማህበራት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ የልማት ድርጅቶችና ሕዝባዊ ድርጅቶች ስትራቴጂውን ተግባራዊ በማድረግና በመገምገም የሚኖራቸውን ሚና በግልጽ ለይቶ የሚሳተፉበትን መንገድ መጠቆም ይገባዋል::

መ) ስትራቴጂው ዘርዘር ባለ መልኩ በተቀረፀ ብቁና ቀልጣፋ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መታገዝ ይገባዋል::

ሠ) የአገር ውስጥ ምርት ሲዋዥቅ በውጭ የመግዛትን አማራጭ ለመጠቀም ስትራቴጂው የውጭ ንግድ ዘርፍ ማጠናከርያ ስልቶችንና እርምጃዎችን በተጠናከረ መልክ ማሳየት ይገባዋል::

## 2. ምርት-ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር

ምርት-ተኮር ሴፍቲኔት የምግብ ዋስትና ስትራቴጂን ሥራ ላይ ለማዋል ከታቀዱት መርሐግብሮች ውስጥ አንዱ ሲሆን የተነደፈውም እ.ኤ.አ. 2004/05 ዓ.ም. ነው:: የመርሐግብሩ ትኩረት ስር በሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ በሚኖሩ ቤተሰቦችና ህብረተሰቦች ላይ ሲሆን አካሄዱም ለምርት መስፋፋት የሚያስፈልጉ ሀብቶችን በቤተሰብ ደረጃ መጠበቅና በማህበረሰብ ደረጃ መፍጠር ነው:: በጥቅሉ ሲታይ የምርት-ተኮር ሴፍቲ-ኔት መርሐግብርና ዓላማ በምግብ ዋስትና ማጣት የተነሳ በረጅም ጊዜ ሊከሰት የሚችለውን የልማት ድቀት መከላከል፣ ቤተሰቦች በማምረትና በመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ተግባራት ውስጥ እንዲሳተፉና የመግዛት አቅማቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዝ ነው::

## 2.1 የምርት-ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር አሠራር

መርሐግብሩ ሁለት ዘርፎች አሉት:: እነሱም ማህበራዊ ሥራዎች (public works) እና ቀጥታ እርዳታ ናቸው:: መሥራት የሚችሉ ነገር ግን ሥር በሰደደ የምግብ ዕጥረት ችግር የተጠመዱ በማህበራዊ ሥራዎች (መንገድ ሥራ፣ ምንጭ ማጎልበት፣ የደን ልማት ወዘተ) በክፍያ እንዲሳተፉ ሲደረግ፣ የመሥራት አቅምና ጧሪ ረዳት ለሌላቸው እና ስር በሰደደ የምግብ ዕጥረት ውስጥ ለሚኖሩት ቤተሰቦች በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ ቀጥታ እርዳታ ይደረግላቸዋል::

## 2.2 የመርሐግብሩ ዒላማዎችና የክፍያው አካሄድ

የመርሐግብሩ ተጠቃሚ መሆን የሚገባቸው አካባቢ ዎች በመርሐግብሩ መስፈርት መሠረት ስር በሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር ውስጥ ያሉና ቢያንስ ላለፉት ሦስት ዓመታት የምግብ እርዳታ ተቀባይ የነበሩ ወ ረዳዎች ናቸው:: ተጠቃሚ ቤተሰቦች የሚመረጡት ቤተሰቡ ላለፉት 3 ዓመታት በተከታታይ የምግብ እርዳታ ተቀባይ የሆነ፣ በከፍተኛ ደረጃ ቋሚ ሀብቱን ያጣ፣ ከዘመድ አዝማድ ምንም ዓይነት እርዳታ የማያገኝ ከሆነና በቀበሌው ኗሪ ከሆነ ነው:: በመርሐግብሩ ተሳታፊ የሚሆኑትን ቤተሰቦች መም ረጥ ላይ የወረዳ የምግብ ዋስትና ግብረ ኃይል፣ የቀበሌ ካቢኔ፣ የቀበሌ የምግብ ዋስትናግብረ ኃይልና የማህበረሰቡ የምግብ ዋስትና ግብረ ኃይል ተሳተፎ እንደሚኖራቸው የምርት-ተኮር የሴፍቲኔት መርሐግብሩ መምሪያ ሰነድ ይገልጻል:: ክፍያን በሚመለከት፣ ሲከፈል የነበረው የቀን ሥራ ዋጋ በነፍስ ወከፍ ስድስት ብር እና በተጨማሪ ወርሃዊ የምግብ ዘይት ነው:: ሆኖም ያለውን የዋጋ ግሽበት በመመልከት በቅርቡ የሥራ ዋጋው ጨምሯል:: የክፍያው ዓይነት በአካባቢው የምርት ገበያ መኖርና ያለመኖር ታይቶ በጥሬ ገንዘብ ወይም በእህል መልክ ነው፤ ማለትም በአካባቢው ያለው የምርት ገበያ ደካማ ከሆነና ማህበረሰቡ በገንዘብ አያያዝና አስተዳደር ያለው ልምድ አነስተኛ ከሆነ ክፍያው በእህል መልክ ሲሆን ሁኔታው በተጻራሪው ከሆነ ግን ክፍያው በጥሬ ገንዘብ ይሆናል::

## 2.3 ተቋማዊ መዋቅርና የመርሐግብሩ አመራር

መርሐግብሩን አቀናብሮ ለመምራትና ሥራ ላይ ለማዋል ከፌደራል እስከ መንደር (community) ደ ረጃ የተዋቀሩ ተቋሞች (ለምሳሌ የፌደራል የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ቢሮ፣ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት፣ የምግብ ዋስትና ግብረ ኃይሎች) አስፈላጊነታቸውን ሰነዱ አስረግጦ ቢገልጽም ተቋሞቹ የጠራ ደንብና አሠራር የላቸውም፤ ተቀናጅተውም አይሰሩም:: አንዳንዶቹ ተቋሞች (ለምሳሌ የቀበሌ ምግብ ዋስትና ግብረ ኃይል) ነፍስ ዘርተው በተገቢው አይንቀሳቀሱም::

## 2.4 የምርት-ተኮር ሴፍቲኔት በጎ ጎኖች

ሀ/ ሴፍቲኔት የምግብ ዋስትና ችግር ሰለባዎችን ካጣዳፊው ችግር ከመታደግ ባሻገር የዘለቄታ የምግብ ዋስትናን ለማበልጸግ ለሚረዱ የምግብ ዋስትና መርሐግብሮች መሠረት ይጥላል::

ለ/ መርሐግብሩ የሕዝብ (public) ሥራዎች በገንዘብ ክፍያ እንዲከናወን ማዘንበሉ መርሐግብሩ የአካባቢን ምርትና ምርታማነትን የማጠናከር ሚናውን እንዲጨምር ያደርገዋል::

ሐ/ መርሐግብሩ ከነፃ እርዳታ አካሄድ ይልቅ ምርትተኮር ሥራ ላይ የተንተራሰ አቅጣጫ መከተሉ ምርታማነትን ለማጎልበት፣ ቋሚ ሀብትን ለማፍራትና የጥገኝነትን መንፈስ ለመከላከል ጠቀሜታ አለው::

መ/ ሌላው አዎንታዊ ጎን ሴቶች የገቢ

ምንጫቸውንና ምርታማነታቸውን እንዲያጎለብቱ ማገዙ ነው፡፡

## 2.5 ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና ጉድለቶች

- ውስን የመርሐግብሩ አቅምና ስፋት በሁሉም አካባቢና ዘርፍ ያለውን የምግብ ዋስትና ችግር ለመቅረፍ ስለማያስችለው ሌሎች ተጨማሪ ስልቶችን መሻት የግድ ያላል፡፡
- መርሐግብሩ በመፍጠር ላይ ያለውን ወይም የፈጠረውን የጥገኝነት አዝማሚያ ከወዲሁ ለመግታት የሚያስችሉትን ስልቶችን መቀየስ ያስፈልጋል፡፡
- በመርሐግብሩ የሚሳተፉት አካሎችና ተቋሞች በተቀናጀ መልክ እንዲሰሩ የሚረዳ መመሪያ አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪም ለተሳታፊ ግለሰቦችና ቡድኖች ተነሳሽነታቸውን ለማበረታታትና ጊዜያቸውን እንዲሰጡ በቂ ክፍያ ወይም ድጎማ መስጠት ለመርሐግብሩ ቅልጥፍና አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡
- በመርሐግብሩ ውስጥ ለሚሳተፉ ቤተሰቦች የሚሰጠው ክፍያ ተመን የአካባቢን ገበያና የኑሮ ሁኔታን ያገናዘበ እንዲሆን ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡
- ከሁሉም በላይ የዳበረ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት መዘርጋት ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ ረገድ መርሐግብሩ የተለያዩ አዎንታዊ ሆኑ አሉታዊ ውጤቶችን መርምሮ ቀጣይ ለሆነ ሥራና ለውጥ የሚያዘጋጅ ዝርዝር የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ማጎልበት ይቀረዋል፡፡ ሌሎች ትኩረት የሚሹ የመርሐግብሩ እክሎች ክፍያዎችን በወቅቱ ያለመክፈልና የመርሐግብሩ አመራር አሳታፊነት፣ ተጠያቂነትና ግልጽነትን አሟልቶ ባለመያዙና ከላይ ወደ ታች የሚወርድ በመሆኑ ለሙስና ችግር መጋለጡ ናቸው፡፡

### የመደምደሚያ አስተያየቶች

የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ መሠረቱ የግብርና ልማትና በግብርና ላይ የተመሠረተ ኢንዱስትሪ ሲሆን በዚህ ትስስር ውስጥ ገበያ ዋነኛ ኃይልና አንቀሳቃሽ ሞተር ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሆኖም መታሰብ የሚገባው ነገር ይህንን ጽንሰ ሐሳባዊ ማዕቀፍ ወደ ተጨባጭና ተግባራዊ ሞዴልና መርሐግብር መለወጡ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ ለስልቱ ተግባራዊነት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ግብአቶችንና ሁኔታዎችን ለይቶ ማወቅ ነው፡፡ ለዚህም በጥልቀት መተንተን የሚገባቸው ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

ሀ) ተነሳሽነት ያለው የሠለጠነና ክህሎት ያለው የሰው ኃይል፤

ለ) በገጠሩ ያለውን ባህላዊ ባህርይና የለውጥ ሂደት መረዳት፤

ሐ) ደንብ ላይ የተመሠረተ የመፈፀም፣ የመከታተልና የመገምገም አቅም፤

መ) ለገበያ ልማት አመቺ ሁኔታዎችን መገንባትና የገበያን መሰናክሎችን በመለየት መፍትሄ መፈለግ፤

ሠ) የግብርናው ህብረተሰብ ለቴክኖሎጂያዊ ለውጥና ለገበያ የማምረት ዝንባሌን እንዲፈጥር ማገዝ፡፡

የመርሐግብሩ አመራርና ውሳኔ አሰጣጥ አጠር ባለ የመዋቅር ዕዝ ሰንሰለት መገደብ ለመርሐግብሩ አፈፃፀም ቅልጥፍና ሊጨምር ይችላል፡፡ በምርት ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር መካተት የሚገባቸውን ቤተሰቦች በመለየት ሂደት ውስጥ በቀበሌና ወረዳ ደረጃ የሚገኙትን የምግብ ዋስትና እጦት ተጠቂ የሆኑትን ቤተሰቦችና መሠረታዊ የገበሬ ማህበራትና ተቋሞችን የማሳተፍ ዒላማ ቤተሰቦችን አጥርቶ ለመለየት ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

በመጨረሻም የምርት ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር በመርሐግብሩ ተጠቃሚ የሆኑ ቤተሰቦች እራሳቸውን ችለው ቀጣይነት ባለው ገበያ-ተኮር በሆነ የአካባቢና የብሔራዊ ኢኮኖሚ ሥርዓት ውስጥ ተቀላቅለው እንዲንቀሳቀሱ የሚረዳ መሆን ይገባዋል፡፡ በዚህ ረገድ ምርት ተኮር ሴፍቲኔት መርሐግብር የቤተሰብና ማህበረሰብን ቋሚ ሀብት ለመገንባት፣ የገበያ ዝንባሌን ለማጎልበት፣ ቴክኖሎጂያዊና ተቋማዊ ለውጥን ለማምጣት አጋዥ በሚሆንበት መንገድ ተስተካክሎ ቢቀረፅ ጠቃሚ ነው፡፡

**ወርቅነህ ንጋቱ (ዶ/ር)**

ምንጭ፡- ታዬ አሰፋ (አርታዒ)፣ «የኢትዮጵያ ብሔራዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና መርሐግብሮች ጥንቅር»፣ ገፅ 1-14፣ አዲስ አበባ፣ ማጥመ፣ 2001 ዓ/ም፡፡


ምስጋናና ማሳሰቢያ

ይህ ሰነድ የታተመው በአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡ ለሰነዱ ይዘት ሙሉ ኃላፊነቱ የደራሲው ሲሆን በምንም ሁኔታ የአውሮፓን ሕብረት አቋም እንደሚያንፀባርቅ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፡፡



አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ (ማጥመ) ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-629 78 88/91♦ ፋክስ: 011-629 78 89
ኢ.ሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et